በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ


**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፱ ዓ.ም.

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1






# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

## መግቢያ

- በዚህ ዘመን እየተቀፈቀፉ ካሉ የክህደት ትምህርቶች መካከል ‹‹ዘ ዳ ቪንቺ ኮድ›› በሚል ርዕስ በዳን ብራውን የተዘጋጀው ልብወለድ መጽሐፍና ፊልም የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- ዘ ዳ ቪንቺ ኮድን ተረፈ አይሁድ በሜል ጊብሰን በ2004 እ.ኤ.አ. ለተሰራው ‹‹ዘ ፓሽን ኦፍ ክራይስት›› ፊልም ክርስትናን ለመበቀል ብለው እንዳዘጋጁት ብዙዎች ያምናሉ፡፡
- ስለዚህ ለዚህ መጽሐፍና ፊልም ፀረ - ክርስትና ይዘት ምላሽ እንደሚያስፈልገው በማመን ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥቂቱ በማዘጋጀት በነሐሴ 1998 ዓ.ም. ካሳተምነው መጽሐፋችን በመውሰድ በምላሽነት አቅርበናል፡፡
- የዳ ቪንቺ ኮድ (The Da Vinci Code) ዳን ብራውን በተባለ እንግሊዛዊ ጸሐፊ የተጻፈ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው፡፡
- ልብ ወለድ መጽሐፉም በተመሳሳይ ርዕስ በፊልም ተዘጋጅቷል፡፡
- ልብ ወለዱ በግድያ ወንጀል ዙሪያ በማጠንጠን ይጀምራል፡፡ ወንጀለኛውን ለማግኘት በሚያደርገው ምርመራ ውስጥ ፀረ - ክርስትና መልዕክቱንና የክህደት ትምህርቱን እናገኘዋለን፡፡
- በልብ ወለዱ ውስጥ የምናገኛቸው ምስጢራውያን ቡድኖችም እርስ በርሱ የሚጋጭ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**መግቢያ**

- ደራሲው ለምስጢራውያኑ ቡድኖች የምሴተ ሐሙስን ጽዋ (Holy Grail) እንደ መረጃ አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል፡፡
- በዚህ ልብ ወለድ መጽሐፉና ፊልሙ ዳን ብራውን ሐሰቱን እውነት፣ ልብ ወለዱን ትክክለኛ አስመስሎ አቅርቧል፡፡
- ጸሐፊው በፈጠራቸው ገጸ ባሕርያትም ሃይማኖታችንንና የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ትምህርቶች ይቃወማል፡፡
- ተቃውሞውም በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በጌታችን መለኮታዊ ኃይል፣ በምስጢረ ሥጋዌ (ተዋሕዶ) እና በሴቶች ጉዳይ ላይ ባለው የተሳሳተ አመለካከቱ ላይ ያተኮረ ሲሆን በመጽሐፉ ሁሉ ልዩ ልዩ የሥጋ ፈቃዳትን በነጻነት መፈጸምን ያበረታታል፡፡
- ዳን ብራውን ክርስቲያን መሆን አለመሆኑን በተጠየቀበት ክፍል የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ‹‹እስካሁን በተለመደው መንገድ ወይም ስሜት ከተወሰደ ክርስቲያን ላልሆን እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ራሴን የበርካታ እምነቶች ተማሪ አድርጌ እቆጥራለሁ፡፡ ብዙ በተማርኩ ቁጥር በርካታ ጥያቄዎች ይኖሩኛል፡፡ መንፈሳዊ ጥያቄዬ በየጊዜው የሚያድግ የዕድሜ ልክ ጥያቄ ነው፡፡›› ብሏል፡፡ ***The Davinci Code*** *፣ ገጽ 341፡፡*

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**መግቢያ**

- የዳ ቪንቺ ኮድ (***The Da Vinci Code)*** በርካታ ታሪካዊ እውነታዎች የተፋለሱበት ከመሆኑ በተጨማሪ ከመሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖታችን የራቁ ልብ ወለድ ሐሳቦች ስብስብ ነው፡፡
- ይሁን እንጂ ጸሐፊው ሥራውን ፍጹም ልብ ወለድ አድርጎ አይመለከተውም፤ ለተጠየቀውም ጥያቄ በሰጠው መልስ የተናገረውም ‹‹በመጽሐፉ የተጻፉት በሙሉ ፍጹም እውነት ናቸው›› በማለት ነው፡፡
- ‹‹ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፡፡ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው፡፡›› ***<u>ዮሐ 8፡31-32</u>***፣ ‹‹ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት፡፡ በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን፡፡››***<u>ቀዳ ጴጥ 3፡15</u>***፡፡ ብለው ቅዱሳን እንደጻፉልን በእግዚአብሔር ፈቃድና ረዳትነት ለደራሲው ተቃውሞዎች ከልብ ወለድ መጽሐፉ በመነሳት ምላሽ እንሰጣለን፡፡
- የደራሲው ተቀውሞዎችም በመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት፣ በጌታችን የባሕርይ አምላክነት፣ በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ፣ በሴቶች መብትና ሥጋዊ ፈቃድን (ፍትወትን) በመፈጸም ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍና ፊልም ምንድን ነው?**

- የዳ ቪንቺ ኮድ ቀልድ አዘል ልብ ወለድ ሲሆን የተጻፈውም በፈረንሳይና በታላቋ ብሪታንያ ያለውን ሁኔታ መሠረት አድርጎ ነው፡፡
- መጽሐፉ ግራ በሚያጋቡ እንቆቅልሾች የተሞላ፣ ወደ ጥርጥርና ክህደትም የሚመራ መልዕክት ያለው ነው፡፡ መጽሐፉም ከ60 ሚሊዮን ቅጂ በላይ ተሸጧል፡፡
- ሰዎች ድብቅ ነው ብለው ያሰቡትን ነገር የመመርመር ጥልቅ ፍላጎት ስላላቸው ይህኑ መጽሐፍ ብዙዎች አንብበውታል ፊልሙንም ተመልክተውታል፡፡
- ገድለው የተሰወሩ፣ ሴራ ወይም አድማ የሚያደርጉ ሰዎች… ቁልፍ ናቸው ተብለው የሚቀርቡ ጉዳዮች የብዙዎችን ትኩረት ለምእተ ዓመታት ሲስቡ ኖረዋል፡፡
- እስካሁን በምናምነውና በምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰወረ ወይም ልንጠራጠረው የሚገባ ምንም ነገር እንደሌለ አብዝተን ማመን ያስፈልገናል፡፡ ካልሆነ ግን ይልቁኑ በዚህ ዘመን የሚሠራጩ ጽሑፎች ወዳልታሰበ ገደል በክህደት ይጥሉናል፤ ያጠፉናልም፡፡
- በዳን ብራውን መጽሐፍ ውስጥም የምናነበው ልብ ወለዱ በጥቂት እውነታ ውስጥ ያጎረውን ግራ አስተሳሰብ ነው፡፡

# <u>የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1</u>

**የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍና ፊልም ምንድን ነው?**

- ጸሐፊው የጽሑፉን አጠቃላይ ይዜት እንደ ልብወለድ አይወስደውም፤ ቢታሰብ ኖሮም ብዙዎችን አይስብም ነበር፡፡
- በሰኔ 1997 (June 2005) የታተመው “Discovery” መጽሔት የዳ ቪንቺ ኮድን መጽሐፍ አስመልክቶ ‹‹የተነገረንን ሁሉ ማመን አይገባንም፤ መጽሐፉ በርካታ ጥያቄዎች ቢያነሳም በበርካታ ሐሰቶች የተሞላ ነው…›› ብሏል፡፡
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ኢየስስም መልሶ፡- እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኵራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜ አስተማርሁ፥ በስውርም ምንም አልተናገርሁም፡፡ስለምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ፥ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው፡፡›› <u>*ዮሐ 18፡20-21*</u>፡፡ እንዳለን እኛም እርሱን የሰሙትን ቅዱስ ማቴዎስን፣ ቅዱስ ጴጥሮስን፣ ቅዱስ ዮሐንስን… ብንሰማቸው እውነቱ እንደተገለጸልን እንዳልተደበቀን እናምናለን፡፡
- በመጽሐፍ ቅዱስ እውነቱ ሁሉ ስለ ተገለጸልን መጽሐፍ ቅዱስን ከነ ትርጓሜው እናንብብ፡፡
- መጽሐፍ ቅዱሳችን አስቀድሞ ‹‹በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ <u>ዘባቾች</u> በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ፡፡›› <u>***2ኛ ጴጥ 3፡3፡፡***</u>

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍና ፊልም ምንድን ነው?**

- ‹‹በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ።።እንግዲህ እናንተ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ።።›› *ካል ጴጥ 3፡16።።*
- ‹‹ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፉ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ፤ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል።።ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም።።›› *ካል ጴጥ 2፡1-3።።*
- ‹‹በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን›› *ቀዳ ጴጥ 3፡15።።* በማለት የነገረን አሁንም ሰይጣን የሃይማኖታችን መሠረት በሆነው በአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚወረወር ፍላጻውን እየሳለ መሆኑን ለመግለጽ ነው።። ሰይጣን የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍን ግራ መጋባትንና ጥርጣሬን በአማንያን ልቦና ለማሳደር የሚያስችለው መሳሪያ አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል።።

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍና ፊልም ምንድን ነው?**

- የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ በገንዘብ ሲተመን ከ250 ሚሊዮን ዶላር በላይ ተሸጧል፡፡ ፊልሙም ከሚያዚያ 1998 ዓ.ም. (May 19, 2006) ጀምሮ ተሠራጭቷል፡፡
- ዳን ብራውን ፈጠራውን ወይም ኑፋቄውን እውነት በማስመሰል ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የክርስትና ሃይማኖታችን ታሪክ የራሱን ሐተታ አቅርቧል፡፡ ልብ ወለዱ በይዘቱ የሚከተሉትን ዋና ዋና የክህደት ሐሳቦች አቅፏል፡፡

1. ‹‹ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ አይደለም፡፡ እውነተኛ አገልግሎቱና ማንነቱ እንኳ በግልጽ ያልታወቀ ተራ ሰው ነበር፡፡››
2. ‹‹ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና መግደላዊት ማርያም ተጋብተው ልጅ ወልደዋል፡፡ ከዚያም በኋላ ወደ ፈረንሳይ ሸሽተው ዘራቸው እስካሁን ድረስ በዚያ ይገኛል፡፡››
3. ‹‹ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መግደላዊት ማርያም የቤተ ክርስቲያን መሪ እንድትሆን ሹሞ ነበር፡፡ ያስተማረው ትምህርቱም እነ ጴጥሮስን በመሰሉ ሰዎች ተሻሽሏል፡፡››

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍና ፊልም ምንድን ነው?**

4. ቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያኖች ይህን እውነት ለ2000 ዘመናት ያህል ደብቀው ኖረዋል፡፡››
5. ‹‹ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔርነት የተለወጠው ፓትርያርካዊ ሂደትን ለመጠበቅ ነው፡፡››
6. ‹‹ብዙ ሚሊዮኖች ስለ ክርስትና ለዘመናት የተሳሳተ መረጃ ሲሰጣቸው ኖረዋል፡፡ በመጨረሻም እነዚህን የተሰወሩ ምስጢራት ያወቁ Sir Isaac Newton እና Leonardo Da Vinci ‘Priory of Sion’ በሚባል ቡድን እየታቀፉ ሥራቸውን እየሠሩ አልፈዋል፡፡ ከእነርሱም Leonardo Da Vinci የደረሰበትን የእውነት ፍንጭ በሳለው የምሴተ ሐሙስ ሥዕሉ ውስጥ አስቀምጧል፡፡
7. ‹‹የጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ማንነትና ምስጢሩን የተረዱ ሰዎች ከ1099 ዓ.ም. ጀምሮ ‘Priory of Sion’ በሚል ድርጅት ታቅፈው የየድርሻቸውን ፈጽመው አልፈዋል፡፡ Sir Isaac Newton እና Leonardo Da Vinci ቀዳሚ ተጠቃሽ የድርጅቱ አባላቶች ናቸው፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**መጽሐፉ የዳ ቪንቺ ኮድ ለምን ተባለ?**

1. የመጀመሪያው ምክንያት ሎዮናርዶ ዳ ቪንቺ በዚህ ልብ ወለድ ውስጥ ስለ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ›› የሚያውቀውን ‹‹እውነት›› ቀንደኛ ገላጭ ሆኖ መቀመጡ ነው፡፡ ‹‹ሊዮናርዶ ዳቪንቺ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የተለያዩ ድብቅ ምልክቶችን (Codes) እንደ መግለጫ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ከነዚህም ድብቅ መልዕክቶች የምሴተ ኀሙስ ሥዕሉ ውስጥ ያካተተው አንዱ ነው፡፡›› ማለቱ ነው፡፡
2. በሥዕሉ ከጌታችን ቀጥሎ በስተቀኝ በኩል የምትገኘው ‹‹መግደላዊት ማርያም ናት፡፡ ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርትና በወቅቱ የተናገረውን ሁሉ በአግባብ የተረዳች እርስዋ ናት›› ስለሚል፡፡ ልብ ወለዱ ይህን ምስጢር የሚገልጽ ነው ሲልም የባለቤቱን ስም እንደ ማስቀደም አድርጎ በማስከተል ‹‹Code›› ብሎታል፡፡

**ጸሐፊው ማነው?**

- በ Exeter, New Hempshire ተወልዶ ያደገ ወላጆቹ ከወለዷቸው ሦስት ልጆች ታላቁ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የ 47 ዓመት ዕድሜ ያለው ጎልማሳ ነው፡፡ ወላጅ እናቱ ሙዚቀኛ የነበረች ሲሆን አባቱ የሂሳብ ትምህርት መርጃ መጻሕፍትን የሚጽፍ የሒሳብ መምህር ነበር፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1

**ጸሐፊው ማነው?**

- በ Amherst Glee Club ውስጥ የዘፈን ግጥም ጸሐፊና ዘፋኝ ሆኖ ሰርቷል፡፡ ‘Synth Animals’ የሚባል የሕፃናት ፊልምና በተጨማሪም “Happy Frogs”፣ “Suzuki Elephants” የሚባሉ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ውስጥ ተሳታፊ ነበር፡፡ በ1991 እ.ኤ.አ በHollywood የዘፈን ግጥም ጸሐፊ፣ አቀንቃኝ (ዘፋኝ)፣ እና ፒያኖ ተጫዋች ሆኖ ተቀጥሯል፡፡ Spanish እና English double major አድርጎ ያጠናቀቀ ሲሆን የ Spanish መምህር ሆኖ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን ያስተምር ነበር፡፡
- Digital Fortress, Deception Point እና Angles and Demons የሚባሉ መጻሕፍትንም ጽፏል፡፡
- ክርስቲያን ስለመሆኑ በተጠየቀበትም ክፍል ‹‹ሦስት ሰዎችን ስለ ክርስትና ሃይማኖት ብትጠይቃቸው አንደኛው ‹መጠመቅ በቂ ነው ይልሃል፡፡›፣ ሁለተኛው ‹የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት መቀበል በቂ ነው ይልሃል፡፡›፣ ሦስተኛው ‹በኢየሱስ ማመን ወይም እርሱን መቀበል በቂ ነው፡፡› ብሎ በየተናጠል ያስረዱሃል፡፡ ሁላችንም የሕይወትን ትርጉም ለማወቅ እንጣጣራለን፤ ራሴን የበርካታ እምነቶች ተማሪ አድርጌ አስባለሁ ወይም እወስዳለሁ፡፡ ብዙ በተማርኩ ቁጥር በርካታ ጥያቄዎች ይኖሩኛል፡፡ ለእኔ የመንፈሳዊነት ጥያቄ የዕድሜ ልክ ጥያቄ ወይም ጌዳይ ስለሆነ ገና ነኝ…›› ብሏል፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 1


## መጽሐፉ ይህን ያህል ታዋቂነት ስለ ምን አገኘ?

- በዓለማችን ውስጥ ስለ ሥጋ ብቻ በሚያስቡና በሚሠሩ ኃነኀሎች እየዳበሩ የሚገኙ የኃጢአት ድርጊቶችን ስለሚያበረታታና ስለሚያደፋፍር ነው፡፡ እነዚህም ድርጊቶች፡-
    1. ራሱን ‹‹የሴቶች መብት›› ተከራካሪ አድርጎ ማቅረብ
    2. የጾታ የፍትወት ፈቃድን ልቅ በሆነ መንገድ መፈጸም
    3. አለመታመንን ወይም ክህደትን ማበረታታት
    4. ‹‹መዳን በዕውቀት ነው›› የሰብአ ፈጠራዎችን (Gnostics) ፍልስፍና ማስተዋወቅ፡፡
    5. ‹‹ኢየሱስ ከብዙዎች አንዱ የሆነ ታላቁ መምህር ነው…›› የሚለውን የ‹‹አዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ›› - “The New Age Movement” አስተምህሮ ስለሚደግፍ፡፡

## ኦርቶዶክሳውያን ለዚህ መጽሐፍ ስለምን ትኩረት ሰጠነው?

1. ጸሐፊው በእውነት ላይ ተመርኩዞ ረጅም መንገድ እንደተጓዘና በመጽሐፉም የተገለጹት ፈጠራዎቹ እንዲሁም መረጃዎቹ ምስጢራትና እውነት እንደሆኑ በመግለጽ ተጽእኖ ለመፍጠርና ለማሳመን ስለሚሞክርና እውነት የሆነውን ማስረዳት ስለሚገባን፤
2. በመጽሐፉ ገጽ 235 ላይ እንደተገለጸው ‹‹በአጠቃላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አባቶቻችን የነገሩን ሁሉ ስህተት ነው ስለሚል የመጽሐፉ ይዘትም የክርስትና እምነታችንን መሠረታዊ ትምህርት ስለሚቃወም ለተጠቀሱት የክህደት ሐሳቦች ምላሽ መስጠት ስለሚጠበቅብን እንደሚከተለው ምላሽ እንሰጣለን፡፡

በርዕሰ
ጉዳዩ
ዙሪያ
ምላሽ
ይሆን
ዘንድ
ታትሞ
የተሰራጨ
መጽሐፍ



# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org